**“አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።”**
**መዝ 118:11**

# የእየሩሳሌም ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን
# <u>የሰንበት ትምህርት አገልግሎት</u>

## የሰንበት ትምህርት ዓላማና ዕቅድ

### <u>ዓላማ</u>

ዓላማችን የሚያሳየን የት መድረስ እንደምንፈልግ ወይም ግባችን ምን እንዲሆን እንደምንፈልግ ነው። ይህም የሚከተሉትን ነጠቦች ያከትታል።

- ልጆች የእግዚአብሄርን አምላክነትና የደህንነት መንገድ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል ምን ማለት እንደሆነ እንዲያውቁ ።
- የሚማሩት ስለ ጌታ ማወቅ ብቻ ሳይሆን በየግላቸው ጌታን ማወቅ እንዲያስችላቸው እና የሚማሩትን በህይወት እየኖሩበት ለሌሎችም የመዳን መንገድ እንዲሆኑ።
- መሠረታዊ የእግዚአብሄርን ሃሳብ በማስተማር ቤተሰብ ወይም ወላጆች በሚዘሩት ቃል ላይ መጨመር ማለትም ለወላጆች ረዳት መሆን ።
- የሰንበት ትምህርት ቤት ለልጆች የሚያስደስታቸው ወይም የሚያሳርፋቸው (trygghet) ቦታ እንዲሆንላቸው ማድረግ።

### <u>ዕቅድ</u>

ዕቅዳችን የሚያሳየን ዓላማችን ጋ ለመድረስ የተለያዩ ሁኔታዎችን(ደረጃዎችን) እንደምናልፍና ምን ማድረግ እንደሚገባን ያሳየናል።

- ለልጆቻችን በህይወታችን፡ በድርጊታችን እና በንግግራችን ምሳሌ እየሆንን ማሳየት።
- የእግዚአብሄርን ቃል እኛ እንደምንረዳው ብቻ ሳይሆን ነገርችን ልጆች በሚያዩበት ዓይን እና በሚረዱበት ቋንቋ እየተመለከትን መጽሀፍ ቅዱስን ከዕለተ ዕለት ኑሮአቸው ጋር በማዛመድ ማስተማር።
- ስለ ልጆች መጸለይ እና ህይወታቸውን መከታተል።
- ከቤተሰብ ጋር የጠበቀ ግንኙነት በማድረግ ስለልጆቸና ስለወደፊት ሁኔታዎች መመከከር።